# አልቆመም ትግላችሁ (ግጥም)

ባችማ ከምስራቅ አፍሪካ

አልቆመም ትግላችሁ፣ እናንት የህዝብ ልጆች፣
መስዋዕትነት በዝቶ፣ ግፍ በደል ቢከማች!
ለፍትህ፣ ለአንድነት፣ ለዴሞክራሲ ሟች!
የህዝቡን ጥያቄ፣ መፈክር ይዛችሁ፣
በዚያ ጨለማ ቀን፣ ስለተነሳችሁ፣
ዘላለም ሕያው ነው! አለ መንፈሳችሁ!
ይቀጥላል ገና! ወደፊት ትግላችሁ!
"ደሜም ይፍሰስና፣ አጥንቴም ይከስከስ!
የሕዝብ እኩልነት፣ የሃገር አንድነት፣ እስኪከበር ድረስ!"
ብላችሁ በወቅቱ፣ ለሕዝብ ዘብ ቆማችሁ፣
መች ይረሳና፣ ያ ጥልቅ ታሪካችሁ።

አልቆመም ትግላችሁ፣ እናንት የሕዝብ ልጆች፣
መስዋዕነት በዝቶ፣ ግፍ በደል ቢከማች!
ለፍትሕ፣ ለአንድነት፣ ለዴሞክራሲ ሟች!

ኢ ወ ክ ድ የሚባል፣ መጠሪያ ይዘናል፣
የእናንተን አደራ፣ ችቦ ተረክበናል፣
መስዋዕትነት ልንከፍል፣ ዝግጁ ሁነናል።
አሉን ጓዶቻችሁ፣ እኛን የፈጠሩ፣
እንደ ሙሴ ሁነው፣ መንገድ የሚመሩ፣
አሉ ጓዶቻችሁ፣ በጽናት፣ በእምነት፣ ለሃገር የቆሙ፣
ለዴሞክራሲ ስርዓት፣ ለሕዝብ እኩልነት፣ ፍትሕን የተጠሙ፣
አሉ ጓዶቻችሁ፣ ምቾት ያልፈለጉ፣
አሉ ጎዶቻችሁ፣ ገንዘብ ያልፈለጉ፣
በአላማቸው ፀንተው፣ በእጅጉ የተጉ፣
ውጣ ውረድ ቢያጥጥ፣ ሳያፈገፍጉ፣
አስከፊውን ስርዓት፣ ቀን ሌት የሚዋጉ።

አልቆመም ትግላችሁ፣ እናንተ የህዝብ ልጆች፣
መስዋዕትነት በዝቶ፣ ግፍ በደል ቢከማች!
ለፍትህ፣ ለአንድነት፣ ለዴሞክራሲ ሟች!
በፍፁም አይቀርም፣ ያ መፈክራችሁ!
ከንቱ ፈሶ አይቀርም፣ ንፁሁ ደማችሁ፣
በታሪክ ሓውልት ላይ፣ ተቀርፆል ስማችሁ። (፬)